በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት

ፕላንና ልማት ቢሮ

የሥነ-ህዝብ ክበባት የአደረጃጀት መመሪያ

ቁጥር 1/ 2018 ዓም

2018 ዓ.ም

ሚዛን አማን

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ የሥነ-ህዝብ ክበባት

የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 1/2018 ዓም

መግቢያ

ፈጣን የሆነ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ለኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ ሀብቶችን በማሟጠጥ ድህነት ሥር እንዲሰድ በማድረግ ለሕዝብ የኑሮ መሻሻል የሚደረገው ጥረት የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ ተጽዕኖ ያደርጋል። በመሆኑም ሁለንተናዊ ልማትን ለማረጋገጥና ብልጽግናን ለማምጣት ዘርፈ ብዙ የሆኑ የክልሉን የሥነ-ህዝብ ችግሮች ደረጃ በደረጃ መቅረፍ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው። ለዚህም ግንዛቤ የሚፈጥሩ ነገን አርቀው እንዲያስቡ ከአቻ ግፊትና ከሱስ እራሳቸውን እንዲጠብቁ በስነ-ተዋልዶ ጤናና ኤች አይቪ ኤድስን ጨምሮ በሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በበቂ ሁኔታ ለተማሪዎች እንዲደርሱ ማድረግ የግድ ይላል። ስለዚህም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ 1ኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ (5-8) እና ሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትምህርት ቤቶች ያሉ ወጣቶችን የሥነ-ህዝብና ልማት እንዲሁም የወጣቱን ሁለንተናዊ የስነ-ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር የስነ-ህዝብ ክበባት እንዲቋቋሙ በማድረግ የወጣቱን የወደፊት ህልሙን እዉን ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 33/2016 **አንቀጽ** 47 **ንኡስ አንቀጽ** (2) ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ሥነ-ህዝብ ክበባት የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 1/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ክልል"** ማለት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ነው።
2. **"ቢሮ"** ማለት የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ነው።
3. "**ክበባት**" ማለት በሥነ ህዝብ ጉዳዮች ላይ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የተደረጃ የሥነ ህዝብ ክበባት ነዉ።
4. **"ጠቅላላ ጉባዔ"** ማለት የሥነ-ሕዝብ ክበባትን በበላይነት ለመምራት የተቋቋመ አካል ነው።
5. **"ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ"** ማለት ከጠቅላላ ጉባኤ ዉስጥ የተመረጡ ክበቡን የሚመሩት የአመራር አካላት ናቸዉ።
6. **"መምህር/ራን"** ማለት በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የመንግስት ሠራተኛ ነዉ።
7. "**ተማሪ**" ማለት በመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ እየተማሩ ያሉ ክፍላቸዉ ከ5ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት ነዉ።

3. የጸታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴት ጸታንም ያካትታል።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

መመሪያዉ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ከ5-12ኛ ክፍል ባሉት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተፈጻሚ ይሆናል።

S/W/B/P/R/S/Planning & Devt Bureau

ክፍል ሁለት

5. ብሔራዊ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ፣የፖሊሲዉ ዓላማ፣ሀገራዊና ክልላዊ ገጽታ እና የስነ-ህዝብ ክበባት አስፈላጊነትና ዓላማ፣

5.1 ብሔራዊ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ፖሊሲ

የብሔራዊ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ፖሊሲ በሚያዝያ ወር 1985 ዓ.ም በሽግግር መንግስት ፀድቆ የወጣ ሲሆን የዚህ ፖሊሲ ዓላማ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔና የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የህዝቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው።ፖሊሲው ትኩረት ከሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ ነው።

5.2 የፖሊሲዉ አጠቃላይ ዓላማ

በዝቅተኛ የምጣኔ ሀብት ዕድገትና በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መሃል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ የህዝብ እድገት ምጣኔን በዕቅድ መቀነስና የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት መቀነስ፤የተፈጥሮ አካባቢን በዘላቂነት ለመጠበቅ የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤የሴቶችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማስወገድ የሴቶች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሣትፋቸውን ማሣደግ፤ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም የሴቶችን፣የወጣቶችን፣የሕፃናትንና አረጋውያንን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ማሻሻል።

6. ሀገራዊ ገፅታ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ በላቲትዩድ መስመር በ 3° እና 14.8'N እና በሎንግቲውድ መስመር 33° እና 48'E አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 1.12 ሚሊዮን ስኩዌር ኪ/ሜ እንደሆነ ይገመታል። የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንቢያ የ2017 ዓ.ም የሀገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ ብዛት 111,652,998 እንደሚሆን ሲገመት ከዚህ ውስጥ ወንድ 55,943,999 (50.1%) እና ሴት 55,708,999 (49.9%) ድርሻ አላቸው። ከአጠቃላይ ሕዝብ ብዛት በገጠር 75.8% እና በከተማ 24.2% የሚኖሩ ሲሆን የህዝብ ጥግግቱ በአማካኝ በ1 ካሬ ኪ/ሜትር መሬት 135 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። (CSA,2017)

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣትነት ሰፋ ባለ ሁኔታ የተተረጎመ ሲሆን ከ15-29 ዓመት ዕድሜ ያለዉን የህብረተሰብ ክፍል ያካትታል። በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኘዉ ወጣት ከጠቅላላዉ የሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር 30% በመቶ ያህል ይሸፍናል። ይህ ወጣት በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሂደቶች ዉስጥ ቁልፍ ሚና ስጫወት ቆይቷል፤እየተጫወተም ይገኛል።እነዚህ የሀገራችንን ህዝብ አብዛኛውን ቁጥር ይዘው የሚገኙት ወጣቶች ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ባህላዊና ሥነ-ልቦናዊ ቀውሶች የተጋለጡ ናቸው። ወጣቶች ለእነዚህ ችግሮች እንዲጋለጡ ያደረጓቸው በርካታ ምክንያቶችን መዘርዘር ቢቻልም በሀገራችን ሥነ-ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ ለወጣቶች የመረጃና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያለመጠናከር (ያለመኖር) በዋነኛነት የሚጠቀስ ምክንያት ነው። አብዛኞቹ ወጣቶች ጠቃሚ ልማዶችን፣ እውቀቶችንና ትምህርቶችን የሚገበዩት ኢ-መደበኛ በሆነው የትምህርት መስክ (Informal Education) አማካይነት ከቤተሰቦቻቸውና ከሚኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብ እንደሆነ ይታወቃል።

ይሁንና ወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤናን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መረጃና የምክር አገልግሎት በመስጠት ረገድ የሚንቀሳቀሱ በጣም ጥቂት የሆኑ አገር በቀልና የውጭ ድርጅቶች ቢኖሩም አገልግሎታቸው በጥቂት አካባቢ የተወሰነ በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ወደ አለው ወጣቱ ዘንድ መድረስ አልቻሉም።በመሆኑም የኢትዮጵያ ስነ-ህዝብ ፖሊሲ ሥራ ላይ ከዋለበት 1985 ዓ.ም ጀምሮ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የወጣቶችን ግንዛቤ በማዳበር ረገድ በፊደራልም ሆነ በክልል ደረጃ አያሌ ጥረቶች አድርጓል። ከዚህ ጥረት ጎን ለጎን ወጣቶች በስነ-ተዋልዶ ጤናና በስነ-ህዝብ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ፣እንዲመካከሩና እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ ለማስቻል በሀገሪቱ በሚገኙ ት/ቤቶች የሥነ-ህዝብ ክበባት ተቋቁመው በመንቀሣቀስ ላይ ይገኛሉ።

7. የክልሉ ህዝብ አጠቃላይ ገጽታ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኢትዮጵያ 11ኛ ክልል ሆኖ 6 ዞኖችን በመያዝና 4 የክላስተር ዋና ከተሞችንና ሁለት ተደራሽ ክላስተር ከተሞችን በመያዝ ህዳር 14/2014 ዓ.ም የተመሰረተ ክልል ነው። ክልሉ በሰሜን አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ በኩል ከጋምቤላ ክልል፣ በስተደቡብ በኩል ከደቡብ ሱዳን እና ደቡብ ኦሞ፣ በስተምስራቅ ከጎፋና ወላይታ ዞኖች፣ በስተሰሜን ምስራቅ ከምባታና ሀድያ ዞኖች ያዋስኑታል። ክልሉ በላቲትዩድ መስመር በ 50° 33' እና 80° 31"N - በሎንግቲውድ መስመር 34° 88' እና 38° 46' E አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን አሁን ባለዉ አደረጃጀት በዉስጡ 6 ዞኖች ያሉት ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 39,061.4 ስኩዌር ኪ/ሜ (3.91 ሚሊዮን ሄ/ር) እንደሚሆን ይገመታል።

S/W/E/P/R/S/Planning & Devt Bureau

የ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንበያ በ2017 ዓ.ም የክልሉ ህዝብ ብዛት 3,956,358 እንደሚሆን ሲገመት ከዚህ ውስጥ ወንድ 1,974,457 (49.9%) እና ሴት 1,981,901 (50.1%) ድርሻ አላቸው። ከአጠቃላይ ሕዝብ ብዛት በገጠር 84.4% እና በከተማ 15.51% የሚኖሩ ሲሆን የህዝብ ጥግግቱ በአማካኝ በ1 ካሬ ኪ/ሜትር መሬት 101 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። ከጠቅላላው የህዝብ ቁጥር አምራች ኃይል (15-64) ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ብዛት 49.65% መሆኑ ከዚህ ውስጥ 28.11% በመቶ የሚሆነው በወጣትነት የዕድሜ ክልል (15-29) የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ።(ፕላንና ልማት ቢሮ 2017)

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ ካለባቸው ክልሎች አንዱ ሲሆን ለዚህም ዋነኛ ምክንያቶች ተብለው ከሚጠቀሱትና በክልሉ ተንሰራፍተው ከሚገኙ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ልጅትን የዝናና የሀብት ምንጭ አድርጐ መቁጠር፣ ዝቅተኛ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት አጠቃቀም፣ ሴቶች በሕብረተሰብ ዘንድ የተሰጣቸው ስፍራ ዝቅተኛ መሆን በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። ከፍ ሲል በአጭሩ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የሕዝብ ብዛት አለመጠን ማደግ በክልሉ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሣድር ይታመናል። ለዚህም እንደምሣሌ የሚጠቀሰው የህብረተሰቡ መሠረታዊ ፍላጐት የሆኑት እንደ ምግብ፣ ንጹህ መጠጥ ውሃ፣ መኖሪያ ቤት የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት፣ ንጹህ አየር የመሣሰሉትን በበቂ እና በጥራት ማግኘት አዳጋች እየሆነ መምጣቱ ነው።

ከፍተኛ ውልደትና ውጤቱ የሆነው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በመማር ዕድሜ የሚገኝ የህዝብ ቁጥርን በመጨመር የትምህርት ፍላጐት እንዲያድግ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የመምህራን ፍላጐት፣የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ እና ቁሣቁስ አቅርቦት የሚጠይቅ በመሆኑ እጅግ ውስን በሆነ የኢኮኖሚ አቅም እነዚህን ለማሟላት ስለማይቻል ይህ ደግሞ በትምህርት ጥራት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በተጨማሪ በመማር ዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች የትምህርት ዕድል እንዳያገኙ ያደርጋል።

8. የክበባት አስፈላጊነት

ወጣቶች በክበባቱ አማካይነት በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ካዳበሩ በጤና መስክ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ትልቅ አጋዥ ይሆናሉ። የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጐለት በአግባቡ ልንጠቀምበት እንድንችል የክበባቱ አባላት በሚንቀሣቀሱበት አካባቢ ማስተማርና መንቀሣቀስ ከቻሉ በግብርና፣በተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ጥበቃ ላይ ለሚደረገው ርብርቦሽ እርሾ በመሆን ያገለግላሉ። እነዚህ ፋይዳዎች ለአብነት ያህል የቀረቡ እንጂ የስነ-ሕዝብ ክበባት ተጠናክረው መንቀሣቀስ ከቻሉ እጅግ ብዙ ጠቀሜታ እንዳላቸው ግልጽ ነው። ስለዚህ ት/ቤቶች የላቀ ሚና ቢኖራቸውም የሥነ-ህዝብ ክበባትን የማጠናከሩ ተግባር በት/ቤቶች ወይም በአንድ የተወሰነ አካል የሚተው ተግባር አይደለምና መንግስትዊና ሰብል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ግለሰቦች ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

9. ስነ-ህዝብ ክበባት አጠቃላይ ዓላማ

ወጣቶች ትምህርታቸውንና ጤንነታቸውን እንዲሁም የወደፊት ኑሮአቸውን የሚያቃውሱ ችግሮችን በመቅረፍ፡ ብቁ ዜጋ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣

9.1 ዝርዝር ዓላማዎች

1. ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ሴት ተማሪዎችን ቁጥር መቀነስ፣
2. ወጣቶች በአካባቢ እንክብካቤ ንቁ ተሣትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
3. የወጣቶችን የሥነ-ተዋልዶ ጤንነትን ለማሻሻልና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት የሚተላለፉትን በሽታዎች መከላከል የሚያስችል ዕውቀት ማስጨበጥ፣
4. ስለ አነስተኛ ቤተሰብ ጥቅምና ይህም ከኢኮኖሚ ጋር በተጣጣመ መልኩ ከአጠቃላይ ከሰው ልጅ ደህንነትና አካባቢ ጥበቃ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ትምህርት መስጠት፣
5. በልማት ፕሮግራሞች ውስጥ የወጣቶችን ተሣትፎ ከፍ ማድረግ፣
6. ወጣቶች ስለፆታ ግንኙነትና ስለቤተሰብ ኃላፊነት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
7. በት/ቤትና በአካባቢያቸው ያሉትን የተዋልዶ ጤንነት (የቤተሰብ ምጣኔ) ምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እንዲጠቀሙ ማድረግና የመሳሰሉት ናቸው።

S/N/B/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

ክፍል ሦስት

10. የስነ-ህዝብ ክበባት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በትምህርት ቤቶችና በክበባት የሚከናወኑ ተግባራት፣

ወጣቶች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ችግሮቻቸውን ለማስወገድ እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ፣ እንዲመካከሩና እንዲወያዩ የሚያስችላቸው አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ማድረግ የስነ-ህዝብ ፖ.ሲ. አንዱ የትኩረት አቅጣጫው በመሆኑ፣በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ወጣቶች በስነ-ህዝብ ክበባት ተደራጅተው ቢማማሩና ሌላውን ቢያስተምሩ የፖ.ሲ.ውን ዓላማ እንዳስፈጽሙ ስለሚቆጠር ወጣቶችና ከወጣቶች ጋር ግንኙነት ባላቸው ሥራዎች ላይ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስነ-ህዝብ ክበባት እንዲደራጁና እንዲታቀፉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

10.1 የስነ-ህዝብ ክበባት አደረጃጀት

የስነ-ህዝብ ክበባት አደረጃጀት በሦስት ይከፈላል

1. የስነ-ህዝብ ክበብ ጠቅላላ ጉባዔ
2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣
3. ቁጥጥር ኮሚቴ

10.1.1 የክበቡ ጠቅላላ ጉባዔ አመሠራረት

ያታና እድሜ ሳይለይ ትምህርት ቤት የሚገኙ የትምህርት ደረጃቸዉ ከ5ኛ ክፍል በላይ የሆኑ ተማሪዎች፣መምህራንና ሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት እንዲሁም ከትምህርት ቤት ውጪ የሚገኙ ወጣቶችና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የስነ-ህዝብ ክበብ አባላት የጠቅላላ ጉባዔ አባል ይሆናሉ።

10.1.2 የክበቡ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት

1. የክበቡ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ሆኖ የመጨረሻ የስልጣን እርከን ውሣኔ ሰጪ አካል ነው፣
2. የክበቡ ጠቅላላ ጉባዔ የክበቡን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል ያሻሽላል አጠቃላይ የክበቡን የልማት ስትራቴጂ ያወጣል።
3. የክበቡን ዓመታዊ ዕቅድ ያዐድቃል አፈጻጸሙን በመገምገም ውሣኔ ይሰጣል፣

የደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ SNNPR/S/Planning & Dev't Bureau

4. የክበቡን የቁጥጥር ኮሚቴ ይሰይማል በተጨማሪም የስራ ሪፖርት በመመርመር ውሣኔ ይሰጣል፣
5. የክበቡን ጠቅላላ ጉባዔ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበስባል
6. እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት 2/3 ከታመነበት ስብሰባ ይጠራል።

10.2 የክበቡ ስራ አስፈሚ ኮሚቴ አመሠራረት

ክበቡን የሚመራው ሰባት አባላት ያሉት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከጠቅላላው ጉባዔ ይመረጡና ከኮሚቴው አባላት ውስጥ የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም እሱ የሚወክለው መምህር የክበቡን ጠቅላላ ጉባዔ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሣቢ ሆኖ ያገለግላል።
የክበቡ ፀሓፊ ደግሞ ከትምህር ቤቱ የተማሪዎች አመራር ወይም የምክር አገልግሎት ኃላፊ የሆኑ ተማሪዎች ቢሆኑ ይመረጣል። የተቀሩት አምስቱ የኮሚቴ አባላት ተማሪዎች ወይም መምህራን ሆነው ከተማሪዎች የሚመረጡ የተማሪ ተወካዮች ሲሆኑ ከእነዚህ የተማሪ ተወካዮች ሦስቱ ሴት ተማሪዎች ወይም ሴት መምህራን ቢሆኑ ይመረጣል።

10.2.1 የክበቡ አመራር ምልመላ መስፈርት

1. የሚመረጡ መምህራን ከክበቡ ዓላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸ የትምህርት ዘርፎችን በማስተማር ላይ የሚገኙ ማለትም የጂኦግራፊ፣የባዮሎጂ፣ሥነ-ዜጋ፣ኢኮኖሚክስና የአካባቢ ሣይንስ መምህራን ቢሆኑ የተሻለ ሥራ ሊሰሩ ይችላል
2. በት/ቤታቸው ውስጥ በስነ-ምግባርና በአርአያነታቸው በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ዘንድ ጥሩ አርአያ የሆኑ ተማሪዎችና መምህራን፣
3. በትምህርት ውጤታቸውም ሆነ በታታሪነታቸው የሚታወቁ፣
4. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የመግባባት ችሎታ ያላቸውና ሌሎችን ለመርዳትና ማስረዳት ፍላጐት ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣሉ።

የደቡብ/ኢ/ሕ/ክ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ S/W/E/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

10.2.2 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

በየትምህረት ቤቶች የሚገኙት የስነ-ህዝብ ክበባት የሚከተሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይኖራቸዋል።

1. ሰብሣቢ
2. ምክትል ሰብሣቢ
3. ፀሐፊ
4. ገንዘብና ንብረት ያዥ
5. የስነ--ህዝብ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪ
6. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ
7. የቁጥጥር ኮሚቴ

የክበቡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብዛትና የሥራ ድልድል በጠቅላላ ጉባዔው እንደሁኔታው ሊሻሻሉ ይችላሉ። ክበቡ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን እንዲረዳውና በይበልጥ አባላቱን ለማሳተፍ እንዲችል እንደ አስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ሊያደራጅ ይችላል።

10.2.3 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

በየትምህርት ቤቶች የሚገኙት የስነ-ህዝብ ክበባት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የክበቡን የቀጣይ ዓመት ዕቅድ ያዘጋጃል በጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣
2. በት/ቤቱ ስለ ሥነ-ህዝብ መረጃና ትምህርት የሚሰራጭበትን ስልት ይቀይሣል፣
3. ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች እየተዘጋጁ የሚሰራጩትን አስተማሪና ቀስቃሽ ቢሮሸሮች፣ፖስተሮችና በራሪ ጽሁፎች በት/ቤት ውስጥና ከት/ቤቶች ውጪ ያሰራጫል፣ ለሕዝብ በግልጽ በሚታይበት ቦታ መለጠፉን ያረጋግጣል።
4. ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስነ-ህዝብና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ድራማና የስነ-ጽሁፍ ውድድር ያዘጋጃል፣
5. በት/ቤት መክፈቻና መዝጊያ ቀናትና በዓላት ላይ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱት አባላት ሽልማት ይሰጣል፣

የፌ/ም/ኢ/ሕ/ከ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ
FMoE/EPRS/Planning & Dev't Bureau

6. በተማሪዎች መካከል የጥያቄና መልስ ውድድሮችን በማድረግ ግንዛቤያቸውን ከፍ እንዲያደርጉ በማድረግ የላቀ ውጤት ላመጡት ሽልማት ይሰጣል፣
7. በየሁለት ወር በመሰብሰብ ሥራዎችን ይከታተላል፣ በየሩብ ዓመቱ ለፕላንና ልማት ጽ/ቤትና ለትምህርት ጽ/ቤት እንዲሁም ለሚመለከታቸው ሁሉ ስለ ክበቡ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያደርጋል፣
8. ኮሚቴዉ ከጤና፣ከትምህርት፣ከግብርና፣ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ፤ ከፋይናንስና ተቋማትና ሌሎች ስብስብ ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመገናኘት ይሰራል።

10.2.4 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስልጣንና ተግባር

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

ሀ. የሰብሳቢው ስልጣንና ተግባር

- የክበቡን ጠቅላላ ጉባዔና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባን ይመራል፣ ያስተባብራል፣
- የኮሚቴውን የስራ ሂደት ይከታተላል፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተላለፉትን ውሣኔዎችን ያስፈጽማል፣
- የአባላቱን የስራ ሂደት ገምግሞ ለኮሚቴው ያቀርባል፣
- ለስራ የሚወጡ ወጪዎችን ያዝዛል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
- ክበቡን በመወከል ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣
- በኮሚቴው የሚሰጡት ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል።

ለ. የምክትል ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

- የኮሚቴው ሰብሣቢ በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ ይሰራል፣
- ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር የኮሚቴውን ሥራ ይመራል፣
- የስነ-ህዝብ ሥራን ለማጠናከር የሚያስችል ጥናት አድርጎ ለኮሚቴ ያቀርባል፣
- በኮሚቴው የሚሰጡት ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፣

ሐ. የፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

- የኮሚቴውን የስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣
- ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር አጀንዳ ያዘጋጃል፣
- የጽህፈት ሥራዎችን ያከናውናል፣

S/W/E/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

- የክበቡን መዝገቦች ፋይሎች እና መረጃዎችን ይይዛል፣
- አባላትን በእድሜና በፆታ ለይቶ ይመዘግባል (የአባላትን መረጃ ይይዛል)፣
- ስብሰባውና ምክትል ሰብሳቢው በሌሉበት ወቅት እነሱን ተክቶ ይሰራል፣
- በየወቅቱ ሪፖርት ያዘጋጃል፣
- በኮሚቴው የሚሰጡት ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፣

መ. የገንዘብና ንብረት ያዥ ስልጣንና ተግባር

- ክበቡ በስጦታ ወይም በልዩ ልዩ ዘዴ ያገኘውን ንብረቶች ኮድና ቁጥር ሰጥቶ መዝግቦ ይይዛል፣ በገቢ መልክ ወይም በልዩ እርዳታ የተገኘውን ገንዘብ ይሰበስባል፣ ይይዛል ኮሚቴው እንዲቀመጥ በወሰነበት ቦታ ያስቀምጣል፣
- የኮሚቴውን ገንዘብ ወይም ንብረት በሊቀመንበሩ ትዕዛዝ ወጪ ያደርጋል፣
- ገንዘብም ሆነ ንብረት በተጠየቀበት ጊዜ ያስመረምራል፣
- በገቢና ወጪ ላይ ሪፖርት እያዘጋጀ ያቀርባል፣
- በኮሚቴው የሚሰጡት ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፣
- ማንኛውንም የክበቡን ንብረት ገንዘብ በሕጋዊ ደረሰኝ ብቻ ያንቀሳቅሳሉ፣
- የንብረት ግዥ የሚከናወነው ከገንዘብ ያዥና ንብረት ያዥ ወጪ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሠ. የትምህርት ቅስቀሳ አስተባባሪ ስልጣንና ተግባር

- በኮሚቴው የስራ ዕቅድ መሠረት የስነ-ህዝብ ትምህርቶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ በኮሚቴ ያፀድቃል
- የተለያዩ የስነ-ህዝብ ትምህርቶች የሚሰራጩበትን መንገዶች ያጠናል፣ የጥናቱም ውጤት ለኮሚቴው አቅርቦ ያፀድቃል፣
- በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ በሚከበሩ የተለያዩ በዓላት ወቅት የቅስቀሳ ስራዎችን ያከናውናል፣
- ለአባላት ትምህርትና ስልጠና በሚሰጡበት ሁኔታዎች ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ የተለያዩ የስነ-ሕዝብ ትምህርት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፣ የማንበቢያ ቦታዎችን ያደራጃል፣
- መረጃዎችን አደራጅቶ ለሚዲያ ተደራሽ ያደረጋል።

S/W/E/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

- ስነ-ህዝብና ልማትን አስመልክቶ ትምህርት ሰጪ ብሮሸሮችን፣ ፖስተሮችን አዘጋጅቶ በገበያ ቦታዎችና ሰዎች በብዛት በሚሰበሰቡባቸው ግልጽ ቦታዎች ላይ ያኖራል፣
- ሌሎች ከኮሚቴው የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል፣

ረ. የመረጃና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

- የክበቡ አማካሪ ሆኖ ያገልግላል፣
- ስለክበቡ በተመለከተ ለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል፣
- ለክበቡ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ያጠናክራል፣
- ክበቡ ከመንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በበላይነት ይመራል፣
- ሌሎች የክበቡ ህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ያከናውናል፣

ሸ. የቁጥጥር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

- የክበቡን ገንዘብና ንብረት ይቆጣጠራል፣
- የክበቡን ገንዘብ ይመረምራል፣ ያስመረምራል፣
- የፋይናንስና ንብረት አወጣጥና አጠቃቀም በክበቡ መመሪያ መሠረት መሆኑን ያጣራል፣
- የክበቡን ገንዘብና ንብረቶች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው መያዛቸውን ይከታተላል፣
- ሌሎች ከቁጥጥር ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ያከናውናል፣

ረ. የክበቡ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሥራ ዘመን

የክበቡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት /2/ ዓመት ብቻ ይሆናል። ሆኖም ጠቅላላ ጉባዔ ካመነባቸው በድጋሚ ተመርጠው ሊሠሩ ይችላሉ፣

የደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ
S/W/E/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

11. በትምህርት ቤቶችና ክበባት የሚከናወኑ ተግባራት

11.1 የትምህርት ቤቶች ተግባራት

1. የክበቡን መቋቋም ጠቀሜታ ለተማሪዎች በመግለጽ አብዛኛዉ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ጥረት ማድረግ፣
2. ክበቡ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም በሚያደርገው እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
3. ከክልሉ፣ከዞኑ፣ከከተማ አስተዳደርና ወረዳዎች ከስነ-ህዝብ ልማት ትምህርት ቅስቀሳ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትና ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ለክበቡ የሚያስፈልገውን የቁሳቁስ ድጋፍ ማግኘት እንዲችል ማድረግ፣
4. የስነ-ሕዝብ ክበብ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተባማጅነት ካላቸው ከሌሎች ክበቦች ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ሊሰራ የሚችልበትን የአሠራር ስልት መፍጠር፣
5. የሴት ተማሪዎች ተሣትፎ እንዲጐለብት የበለጠ ጥረት ማድረግ፣
6. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በስነ-ህዝብና ልማት እንዲሁም በተባማጅ ርዕሶች ላይ በተማሪዎች መካከል ውድድሮች እንዲካሄዱ ማበረታታት እንዲሁም አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
7. የስነ-ህዝብና ልማት ትምህርቶችና መረጃ በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ መገናኛ ዘዴዎች በሰፊው እንዲሰራጨ ማድረግ የት/ቤቱ የሚኒ-ሚዲያ ሴንተር መጠቀም፣
8. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የስነ-ህዝብ ክበብ አባላት ለማንበቢያ እና ለውይይት የሚሆናቸውን ቦታዎችን ማዘጋጀት፣
9. ከክበቡ አባል ተማሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር የሚችሉ ከተማሪዎች ጋር ለመስራት ፍላጐትና ፈቃደኝነትን የሚያሣዩና የተማሪዎችን ግላዊ ችግር በማዳመጥ መፍትሔ ለመፈለግ ገፃጅ የሆኑ መምህራንን በመምረጥ የክበቡ መሪ ማድረግ፣
10. በስነ-ህዝብ ክበብ ውስጥ የሚሣተፉ ተማሪዎች በማይማሩበት ፈረቃ ስለሚያካሂዷቸው ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ወላጆቻቸው አውቀው እንዲፈቅዱና ተገቢውን እገዛ እንዲያደርጉ ትምህርት ቤቱ ለወላጆች ስለክበብ እንቅስቃሴና ጠቀሜታ ስለልጆቻቸው ተሣትፎ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፣

የደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ
SNNPR/S/Planning & Dev't Bureau

11. የትምህርት ቤቱ የወላጅ መምራን ህብረት በትምህርት ቤቱ ለተቋቋመው የስነ-ህዝብ ክበብ የትምህርት መሣሪያዎች፣ ቁሳቁስ እና በጀትም ቢሆን በመደገፍ እንቅስቃሴውን ማበረታታት ይጠበቅበታል።

12. የስነ-ህዝብ ክበብ እንቅስቃሴን አስመልክቶ የሚተገበሩ እንደ እስፖርት ውድድር፣ልዩ ልዩ በስነ-ህዝብና ሥነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ያተኮሩ ትምህርታዊ የጥያቄና መልስ ውድድሮችን ማዘጋጀት፣

13. በወላጅ ቀን፣ በትምህርት ቤቱ ስብሰባዎች፣በበዓላት ቀናት ወዘተ... በስነ ሕዝብ ጉዳዮች ዙሪያ መቅረብ ያለባቸው ርዕሶችን በመምረጥ ክበቡ ትምህርታዊ መልዕክቶችን እንዲያስተላልፍ ማድረግ

14. በትምህርት ቤቶች በየ15 ቀናት ለ 1 ሰዓት የክበባት ቀን እንዲሆን በመወሰን የተለያዩ መልዕክቶች፣ ወይይቶች፣ጭዉዉቶችና ድራማዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፣

11.2 በክበባት የሚከናወኑ ተግባራት

1. ከኢኮኖሚ አቅም ጋር የተገናዘበ የቤተሰብ ብዛት ጠቀሜታ፣ስለ አካባቢ ጥበቃና ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በአካባቢ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ በቂ መረጃ መስጠት፣
2. በት/ቤቶችና ከት/ቤቶች ውጭ ለሚገኙ ወጣቶች ስለ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነትና ውርጃ፣አባላዘር በሽታዎችና በተለይም ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አደገኛነትና የመከላከያ ዘዴዎች ማስተማር፣
3. የወጣቶች ስነ-ልቦናዊ ችግሮችና ጎጂ ልምዶችን ለማስወገድ የሚያስችል የምክር አገልግሎት በት/ቤቶችና ከት/ቤቶች ውጭ ለሚገኙ ወጣቶች መስጠት፣
4. በአካባቢው ለሚገኝ ህብረተሰብ ስለ ሥነ-ህዝብና አካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ ማስጨበጥ
5. በክበባት አባላት መካከል የእርስ በርስ ውይይትና ምክክር ልምድ ማጎልበት፣
6. በየአመቱ የሚከበሩትን የዓለም የሥነ-ህዝብ ቀን፣ የአካባቢ ቀንና የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቀን ወጪ በማይጠይቁ የተለያዩ ዝግጅቶች ለምሣሌ በትግኝ ተከላ፣ በጽዳት ዘመቻ ወ.ዘ.ተ ማክበር፣
7. በስነ-ህዝብና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የውይይትና የክርክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣
8. ክበቡ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ሌሎች ተማሪዎች እንዲያውቁዋቸው ማድረግ፣

ክፍል አራት

12 የማስፈፀሚያ ስልቶች፣የገቢ ምንጭ፣የክትትል፣ግምገማና መረጃ አያያዝ ስርዓት

12.1 የተግባራቱ ማስፈጸሚያ ስልቶች

1. የትምህርት ቤት ሚኒ-ሚዲያን በመጠቀም አጫጭር መልዕክቶችን ማሠራጨት፣
2. በድራማና በትያትር፣ በፊልምና ስነ-ጽሁፍ ውድድር መጠቀም፣
3. በውይይት እና በሰልፍ ላይ የስነ-ሕዝብና ልማት ትምህርታዊ መልዕክቶችን፣ መገለጫዎችንና ዘፈኖችን በመጠቀም፣ በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪም ፕሮግራም በማስያዝ በክበቡ አባላት ለተማሪዎችና ለአካባቢው ህብረተሰብ ማስተማር፣
4. ተማሪዎችን በየክፍሉ በቡድን ሆነው እንዲወያዩና እንዲከራከሩ እንዲሁም ክፍል ከክፍል ጋር እንዲፎካከሩ ማድረግ፣
5. በስነ-ህዝብና ልማት ዙሪያ እውቀት ያላቸው በአካባቢው የሚገኙ ምሁራንና ባለሙያዎችን በመጋበዝ ትምህርትና ገለፃ እንዲያደርጉ ማድረግና የት/ቤቱን ህብረተሰብ የሚያሳትፍ የፓናል ውይይት ማዘጋጀት፣
6. በስነ-ህዝብና ተዋልዶ ጤና፣ በስርዓተ ፆታ፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ፣የኤች አይ ቭ/ኤድስ ቀን፣የዓለም ስነ-ህዝብ ቀን ወ.ዘ.ተ. የመሣሰሉት የተለያዩ በዓላት በሚከበሩበት ቀናት ላይ ማስተማርና መቀስቀስ፣
7. የተለያዩ ፖስተሮች፣ በራሪ ጽሁፎችን፣ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም በብዙሃን መገናኛ የሚተላለፉ መልዕክቶችን በመጠቀም ማስተማር፣
8. የወላጆች፣ ቀንን በመጠቀም ለክበቡ አባላት ሰፊ ቅስቀሳዎችን በማድረግ ወጣቱን ማስተማር፣
9. የትምህርት ቤቱን የማስታወቂያ ሠሌዳ በመጠቀም በወጣቶች የተዘጋጁ የተለያዩ ስዕሎችን፣ ካርቱኖች፣ ጽሁፎችን እንዲሁም የሳምንቱን፣ የወሩን፣ የዓመቱን ምርጥ ሥራዎችን (መፈክሮችን) አዘጋጅቶ ማሠራጨት የብቻ ውይይት ፕሮግራም አዘጋጅቶ በማስተማርና በማሰልጠን ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ የሴት ተማሪዎች የአካባቢውን ሴቶችና እናቶችን እንዲያስተምሩ ልዩ እንቅስቃሴ ማድረግ፣
10. የወጣቶች ማዕከላት፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሰጪ ማዕከላትንና የተለያዩ በቅርበት ያሉ ትምህርት ቤቶች የስነ-ሕዝብ ክበባት እንቅስቃሴን በማስጐበኘት ልምድና ዕውቀት እንዲያገኙበት ማድረግ፣

የደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ጥላንና ልማት ቢሮ
SNNPR/Population & Dev't Bureau

11. በአካባቢው ከሚገኙ የጤና ኤክስቴሽን ሠራተኞች ጋር ተቀናጅተው ህብረተሰቡን ቤት ለቤት ለማስተማር ዕቅድ አውጥቶ መንቀሣቀስ፣
12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በት/ቤታቸው የስነ-ህዝብ (mini-exhibition) ማዘጋጀት፣
13. በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ይሳተፉ የነበሩ ግለሰቦችን በማስተማርና ከራሳቸው የጐጂ ልማዳዊ ድርጊት አስወጋጅ ኮሚቴ አድርጎ በማደራጀት መጠቀምና ለተማሪዎችም እንዲያስተምሩ ማድረግ፣
14. ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና ከሌሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የስነ-ህዝብ ትምህርት ሬዲዮ ስክሪፕት አዘገጃጀት ላይ ለተማሪዎች ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በተማሪዎች የሚዘጋጁትን ጽሁፎች በት/ቤቱ ሚኒ-ሚዲያ አማካይነት ማስተላለፍ፣
15. በት/ቤቱ ውስጥ ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመነጋገር የስነ-ህዝብና ልማት ትምህርታዊ መልዕክቶችን የያዙ የተለያዩ ጽሁፎችን ማስቀመጫና የንባብ ቦታ (Mini/ሚኒ/ላይብራሪ) ማዘጋጀትና በተማሪዎች እንዲነበቡ ማድረግ፣
16. ከሌሎች ት/ቤቶች ከሚገኙት የስነ-ህዝብ ክበባት ልምድ በመውሰድ የሴት ተማሪዎች በክበቡ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራንና መምህራን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

12.2 የክበባት ተባባሪ ድርጅቶች፣ የገቢ ምንጭና፣ ንብረት አስተዳደር

የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ሥራ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ የሚመለከት መሆኑ በስነ-ህዝብ ፖሊሲው ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። ስለዚህ የስነ-ህዝብ ክበብ የስነ-ህዝብ ጉዳይ የሚመለከታቸው በአካባቢው ያሉትን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን በስነ-ህዝብ ፕሮግራሞች ላይ በማሳተፍ እንቅስቃሴያቸውን ማጠናከር አለባቸው። ለምሣሌ የጤና ድርጅቶች ስለቤተሰብ ዕቅድ ለማስተማርና ለምክር አገልግሎት ... ወዘተ በመስጠት የሙያ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሌሎችም እንደ ግብርና ቢሮ፣ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ትምህርት፣ ጤና ቢሮዎች/መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች ወዘተ... በዕቅዶቻቸው ውስጥ የስነ-ህዝብ ጉዳይ የተካተተ ስለሆነ እነዚህ ተባባሪዎች ጋር ሥራን ማቀናጀት ይቻላል። በተጨማሪም የስቨል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለስነ-ህዝብ ፖሊሲ ተግባራዊነት ሕብረተሰቡን ለማስተማር በድርጊት መርሃ ግብራቸው ውስጥ አካተው መስራት ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ድርጅትን በክበቡ እንቅስቃሴ ውስጥ የራሳቸዉ ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠቅማል።

12.2.1 የክበቡ የገቢ ምንጭ

ክበቡ እራሱን ለማጠናከር እንቅስቃሴውን ለማጐልበት እንዲረዳው የራሱ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፡፡በዚህ መሠረት የክበቡ ዋነኛው ምንጭ የክበቡ አባላት ይሆናሉ፡፡እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የክበቡን ገቢ ማጐልበት አስፈላጊ ነው፡፡ ከልዩ ልዩ መንግስታዊ፣ ስብስብ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግል ድርጅቶችና ከንብረተሰቡ የቁሳቁስም ሆነ የገንዘብ እርዳታ የሚገኝበትን ዘዴ መፈለግና መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴና ቅስቀሳ ማካሄድ ውጤቱን የተሻለ ያደርገዋል፡፡

12.2.2 የንብረት አስተዳደር

ማንኛውም በክበቡ ስም የሚገኝ ገንዘብም ሆነ ንብረት ስርዓት ባለው መንገድ መመዝገብ አለበት፡፡ የገንዘብና የንብረት አያያዝና አጠቃቀም የትምህርት ቤቱን የፋይናንስ አጠቃቀም ሥርዓትና ደንብ የተከተለ ሆኖ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለስራው አስፈላጊ የሆነው ገንዘብና ንብረት ከትምህርት ቤቱ ጋር በመመካከር ሥራ ላይ ያውላል፡፡ንብረትን በሚመለከት ቋሚና አላቂ ንብረቶችን ለይቶ በመመዝገብ አላቂውን በስነ-ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡ የንብረትና የገንዘብ አጠቃቀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመሆን በየወቅቱ አዲት እየተደረገ የአዲት ሪፖርት መቅረብ አለበት፣

13 የክበባት መረጃ አያያዝ፤ክትትልና ግምገማ ስርዓት

13.1 የክበባት መረጃ አያያዝ

በት/ቤቶችና ከት/ቤቶች ውጭ የሚቋቋሙት የስነ-ህዝብ ክበባት የሚያከናውኗቸው ሥራዎች በመረጃ መያዝና ማከማቸት ያስፈልጋል፡፡በዚህ መሰረት

1. የዓመቱን ሥራ ዕቅዶችና የተከናወኑ ስራዎች በየዕቅድና የክንውን ጊዜያቸው በመለየት መረጃዎችን መያዝ፣
2. በየዓመቱ በክበቡ ውስጥ ያሉ የአባላት ዝርዝር በየታ፣ በእድሜ በመ.ያ ለይቶ መመዝገብ፣
3. አባላት የተሰበሰቡበትን ኘሮግራሞችና ብዛታቸውን በየታና በመ.ያ ተለይቶ መረጃ መያዝ፣
4. ቋሚ የስብሰባ ቀናት፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ቅጾችን ወዘተ... በጥንቃቄ ማዘጋጀትና በአግባቡ መያዝ፣

5. በየዓመቱ የተከናወኑትና ያልተከናወኑት ሥራዎች ተለይተው ሁልጊዜ መረጃቸው መያዝ አለባቸው። በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ክበብ መረጃዎች በአግባቡ በማደራጀት ማስቀመጥና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፣

13.2 የክትትል ሥርዓት

የት/ቤቶች የስነ-ህዝብ ክበባት በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ተግባራትና የአፈጻጸም ስልቶች በታቀዱት ዕቅዶች መሠረት ከግብ ለመድረስ መከናወን አለመከናወናቸውን ለማረጋገጥ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የክትትል ሥርዓቱ ማጠናከር ነው። በመሆኑም፡-

1. በክልሉ በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር መዋቅሮች ማለትም በክልል፣ በዞን ወረዳ እና ከተማ አስተዳሮች ባሉ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የክበባቱን እንቅስቃሴ በቅርበት ይከታተላሉ።
2. የትምህርት ቤቶች የስነ-ህዝብ ክበባት እንቅስቃሴ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ በዓመት 4 ጊዜ ክትትል ያደርጋሉ።
3. በየሩብ ዓመቱ የትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች የስነ-ህዝብ ክበብ እንቅስቃሴ ክትትል በማድረግ ሪፖርት ይቀበላሉ፣ ለሚመለከተው ክፍልም ያስተላልፋሉ፣
4. በክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ በየዓመቱ ለሁለት ጊዜ የትምህርት ቤቶች የስነ-ህዝብ ክበባት አፈጻጸም የመስክ ግምገማ ይካሄዳል።

13.3 የግምገማ መስፈርት

የክበባት የመገምገሚያ መስፈርቶች

1. የስነ-ህዝብ ክበቡን በዕቅድ የመምራት ችሎታ፣
2. የክበቡ አመራር ጥንካሬ፣
3. በዓመታዊ ዕቅዳቸው መሠረት ያከናወኗቸውን ተግባራት ስኬታማነት፣
4. የክበቡ አባላት ዘንድ ውይይት የተደረገባቸው የስነ-ህዝብ ጉዳዮች ብዛትና ጥልቀት፣
5. የክበቡን አባላት በዕድሜ በፆትና በክፍል ደረጃ ከፋፍሎ መረጃ የመያዝ አቅማቸው፣
6. ከሌሎች ክበባት ከሚኒ ሚደያ፣ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ አካባቢ እንክብካቤ ከሴት ተማሪዎች ወዘተ ጋር ያላቸው የተቀናጀ የአሰራር ሁኔታ፣
7. የስነ-ህዝብ ጉዳዮችን በተለያዩ ስነ-ጽሁፋዊ ቅርጽ/ግጥም፣ ድራማ፣ ልበ-ወለድ፣ ጭውውት፣ ትረካ ለማቅረብ ያደረጉትን ጥረት እና፣

8. ሌሎች ክት/ቤቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ መመዘኛዎችን እንደ ግምገማ መስፈርት መጠቀም ይቻላል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. ስለመተባበር ግዴታ

❖ የባለድረሻ አካላት፣ አስፈጻሚ አካላት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

16. ተጠያቂነት

❖ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፤

17.መመሪያውን ስለ ማሻሻል

❖ ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል።

18.ተቀባይነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

❖ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

19. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ፀድቆ ከወጣበት ቀን--------2018 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ወ/ሮ ወሰነች ቶማስ

የፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ

ሚዛን-አማን